# የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ -
# በ97ቱ ቅንጅትን፣ በ2002ቱ...?

ፍሬነህ ደረጀ

በአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ላይ እና የህዝቡን ነፃ ምርጫ በተመለከተ በግሌ የሚሰማኝንና ቢሆን ጥሩ ነው ብዬ የማስበውን ለመግለፅ በማሰብ ነው ይህንን ፅሁፍ ለመጻፍ ያነሳሳኝ፡፡(ምንአልባት ለንባብ ቢበቃም ባይበቃም ይነስም ይብዛም እንደ አንድ ዜጋ ሀሳቤን መግለፅ አለብኝ፡፡) ፅሁፉ በአብዛኛው አገር ቤት ውስጥ ያለውን ህዝብ ቢመለከትም ትግሉ የጋራ እንደመሆኑ መጠን የሁላችንንም ትብብር ይጠይቃል፡፡

የ97ቱን ምርጫ በተመለከተ ሁላችንም ጠንቅቀን ስለምናውቀው ተጨማሪ መግለፅ አያስፈልግም፡፡ ነገር ግን ወደሁዋላ 5ዓመታት ተመልሰን ስለነበረው የ92ቱ ምርጫ በተለይ እኔ በአካባቢው በስራ ምክኒያት ስለነበርኩበት የሃዲያ ዞን ምርጫ ያየሁትንና የሰማሁትን መግለፅ እወድዳለሁ፡፡

የሃዲያ ዞን በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በዞኑ ውስጥ ወያኔ የፈጠረው ድርጅትና የተቃዋሚው በዶ/ር በየነ ጴጥሮስ የሚመራው ፓርቲ ያለበት ነው፡፡ ታዲያ በዚያን ወቅት በዚህ ዞን በተደረገው ምርጫ በህዝቡ ላይ የደረሰው ጉዳት- በሰው ህይወት መጥፋት፣ የጅምላ እስር፣ በመሳሰሉት በአይነቱና በይዘቱ ከ97ቱ ምርጫ ጋር ፍፁም ተመሳሳይ ሲሆን ልዩነቱ የ97ቱ ምርጫ ትልቅ ትኩረት ያገኘና አለም አቀፍ ይዘት የያዘ በመሆኑ ብቻ ነው፡፡

ህዝቡ የምርጫ ሳጥኑን አላዘርፍም ብሎ በመከላከሉ በፈጥኖ ደራሽ ወታደሮች መከራውን አይቶአል፡፡ በውድድሩ ያሸነፉት ተመራጮች- መለስ ዜናዊን በማንሳት በበየነ ጴጥሮስ እንተካዋለን ብለው ሲማከሩና ራሳቸውንም በየሚኒስቴርነት ሲሾሙ ተገኝተዋል በሚል ሃሰተኛ ክስ ተወንጅለው ታፍሰው ታስረውበታል፣ ተደብድበውበታል፣ በአንድ ወረዳ የነበረ ታዛቢ አስመራጭ ከነባለቤቱ በቦንብ ተገድለውበታል፣ ፈጥኖ የተባለ አረመኔ ጦር በአካባቢው በመስፈር ሰላማዊ ሰዎችን ገድሎበታል፣ የአካባቢው ገበሬ ማዳበሪያ ሲጠይቅ በየነ ጴጥሮስን ጠይቁት የመረጣችሁት እርሱን ነው እርሱ ያቅርብላችሁ ተብለው መከራ አይተውበታል፣ የመንግስት ሰራተኞች የሰሩበትን ደሞዝ ሲጠይቁ ህዝቡ ለወያኔ ግብር አልከፍልም ስላለ የሚሰጣችሁ ገንዘብ የለም ተብሎ ከሶስት እስከ ስድስት ወር ያለ ደሞዝ ተቀጥቶበታል፣ ለዞንና ለክልል የተመረጡ ተመራጮችን ጨምሮ በርካታ የክልሉ ምሁራን፣ ገበሬዎች፣ ተማሪዎችና ንቁ ተሳትፎ ያሳዩት በሙሉ በሆሳእና ወህኒ ቤት ታጭቀው ከሰነበቱ በሁአላ እያንዳንዳቸው << በይቅርታ>> ደብዳቤ ላይ ፈርመው ተለቅቀዋል፡፡

በወቅቱ ወያኔ ይሄ ይመጣብኛል ብሎ ስላላሰበ የምርጫው ውጤት ሰው በሚያየው ቦታ ሁሉ እንዲለጠፍ አዝዞ ነበርና በከተማው ፖሊስ ጣቢያ በር ላይ የተለጠፈውን ለማየት ችዬ ነበር፡፡ ጠቅላላ የወያኔ ተመራጮች ያገኙት ድምፅ ከ10 ድምፅ በታች ሲሆን የተቃዋሚው ግን ከ100ዎች በላይ እንደነበር ልብ ብዬ ነበር፡፡ በሰአቱም የወያኔውን ተመራጮች የመረጡአቸው የራሳቸው ቤተሰቦች ብቻ ናቸው ተብሎ ሲቀለድ ነበር፡፡ ሁኔታዎች በደቂቃ ተለዋወጡ፡፡ የምርጫው ውጤት ወዲያው ተገንጥሎ ተነሳ፡፡ አቶ መለስ ማታውኑ ገብቶ ሌሊቱን ተመልሶ ሄደ ተባለ፡፡ ከዚያማ ሁሉ ነገር ከላይ እንደገለፅኩት ነው፡፡ በዶ/ር በየነ በኩል የታየ ተቃውሞ በዝርዝር ባላውቅም በአደባባይ ይየሁት ግን- 1ኛ፡- ከምርጫው በሁአላ አካባቢውን ለመጎብኘት ሲመጡ የአካባቢው ሰው የመሪ አቀባበል ካደረገላቸውና ( በግልፅ መኪና የአበባ ጉንጉን አድርጎላቸው እጃቸውን እያውለበለቡ) በሽማግሌዎች ተመርቀው ንግግር አደረጉ፡፡ በንግግራቸውም ከዚህ ጠንካራ ህዝብ በመወለዴ እኮራለሁ አሉ፡፡2ኛ፡- ከምርጫው በሁአላ ምክር ቤቱ ሲከፈት ስብሰባውን ከመጀመሩ በፊት በዚሁ ምርጫ ውዝግብ በዞናቸው በወያኔ መሪዎችና የፈጥኖ ወታደሮች ህይወታቸው ላለፈው ዜጎች የህሊና ጸሎት ጠየቁላቸው፡፡ የወቅቱ አፈ ጉባኤ አቶ ዳዊት ዮሃንስ በችኮላ ፈቀዱና የኸው ተደረገ፡፡(የወያኔው መሪ ዲሞክራሲን ለማምጣት ከደርግ ጋር ሲፋለሙ ህይወታቸውን የሰዉ ብዙ ሺህ ታጋዮች ሳይደረግላቸው በራሳቸው ጥፋት ህይወታቸውን ላጡት ሰዎች የህሊና ፀሎት መደረጉ እንዳስቆጣቸውና ለወደፊቱም ጥንቃቄ እንዲወሰድ የሚል መልዕክት ያለው ንግግር

አደረጉ። ወ/ሮ ገነት ጉዲት ደግሞ ጥቂት ሰዎች ሞቱብኝ ብለው ከአሁኑ መስዋትነትን አይፍሩ ብለው ዶ/ሩ ላይ ተሳለቁ።) የሃዲያ ህዝብም ድምጼን አላስነጥቅም ብሎ ህይወቱን ጭምር የሰዋለት ምርጫ ዶ/ር በየነንና ጉዋደኞቹን ብቻ ም/ቤት በመከተት የቀሩትን ተመራጮቹን በወህኒ ቤትና በስደት ራሱን ደግሞ ላልተቋአረጠ የመንግስት ጉንተላና ዱላ አትርፎ ሌላ ለውጥ ሳይመጣለት ቀረ።

በ92ቱ ምርጫ በሃዲያ ዞን (ሌሎችም ተመሳሳይ ዞኖች ይኖራሉ) በ97ቱ ምርጫ በአገር አቀፍ ደረጃ እየተዘረረ በመፈንቅለ መንግስት የሚገዛው ወያኔ አሁን ደግሞ በ2002ቱ ምርጫ የምርጫ ኮሮጆዎቹን በስሙ አጭቆ (ከተቃዋሚዎችም ማን ከማን ወረዳ አሸንፎ ም/ቤቱ እንደሚገባ ወስኖ) ቀን እየጠበቀ ያለበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። አሁን የሚቀረው ምርጫውን ለቀሪው አለም ትክክለኛ ማስመሰል ብቻ ነው። ለዚሁም የፓርቲዎች የስነ ምግባር ደንብ የሚል በማስፈረም 65 ፓርቲዎችን የተወዳጁት ሲሆን ላልፈረሙትም ፓረቲዎች አባሎቹን በአስተማማኝ ስላስገባ (ስለገቡ) እርስ በእርስ እየተነታረኩ እንዲጠብቁት አድርጎአል።

እንግዲህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ ምንድን ነው?

ከወያኔ በኩል በማስፈራራትም ሆነ በማንኛውም ዘዴ ስልጣን ከእጁ እንደማይወጣ እየዛተ ነው። ከተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚሰማው ደግሞ፡- 17 ዓመት በጠመንጃ ታግሎ የመጣ ስለሆነ በምርጫ መጣል ስለማይቻል ውስጡ ገብቶ መታገል ይበቃል፣ ከእንግዲህ የዲሞክራሲያዊ መብቴ አልተጠበቀልኝም የሚል ሰው መኖር የለበትም፣ ሰላማዊው መንገድ ረጅም ጊዜ ስለሚፈጅ በትዕግስት መጠበቅ ያስፈልጋል፣ የህግ የበላይነት ጉዳይ የግለሰብ ጉዳይ ስለሆነ እኛን አያገባንም (መንግስትን ከሚያስቆጣ ተግባር የተቆጠብን ነን።) ወዘተ...ነው። ይህ ከሆነ ዘንድ ህዝቡ ይህንን ምርጫ ባይሳተፍ ምን ይመጣበታል? ችግሩ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችን ማስመረጥ ስላልሆነ በደንብ ሊታሰብበት ይገባል። ለነገሩ ተቃዋሚዎችንም ለማስመረጥ የሰው ህይወት መገበር የግድ የሆነ ይመስላል። የህዝቡን ብሶት የሚያሰማ የፖለቲካ መሪ ወይንስ ስለህግ የበላይነትና የህዝብ ነፃነት አብሮ የሚታገል የህዝብ መሪ? ምርጫችን ሁለተኛው እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለኝም። ይህ ከሆነ ዘንድ እነዚህ የህዝብ መሪዎች ከየት ነው የሚመጡት? ግማሹ ተሰድዶአል፣ ግማሹ በአገር ቤት አለ፣ ግማሹ ደግሞ በወያኔው እስር ቤት ውስጥ ነው። ወያኔ አገር ቤት እንደገባ ሁሉንም በብሄር ብቻ እንዲደራጁ ፈቅዶ በሚያዋክብበት ሰዐት የሰብዐዊ መብት ድርጅት አቁዋቁመው የህዝቡን ነፃነትና ሰብዐዊ መብት ሲያስተምሩና ሙያዊ ትንተና ሲያቀርቡ የነበሩትን ትተን በአሁኑ ወቅት በምንም መንገድ ለደቂቃም ልንዘነጋት የማይቻለንን ብርቱካንን ማንሳት አለብን። በዚህ ወቅት ወደድንም ጠላን ትግላችን ከእርስዋ ጋር አስተሳስሮናል።‹‹ ብርቱካን ሳትፈታ ምርጫ ውስጥ መግባት የለብንም።›› ይህ አላማ ሊያስተሳስረን ይገባል። በዚያውም ብርቱካን የታሰረችበትን ምክኒያት እንመርምር።

ብርቱካን ለምን ታሰረች? ለምንድነውስ የወያኔው መሪ እርስዋን ለማስፈታት በምንም ዓይነት ድርድር አይኖርም ያለበት ምክኒያት? (በነገራችን ላይ የብርቱካን ከእስር ቤት ውጭ መሆን የራሱን እድሜ የሚያሳጥርበት ስለሚሆን ከምርጫውም በሁዋላ ቢሆን ይፈታታል የሚል ምንም ሀሳብ የለኝም።) እርስዋን ያሳሰረው ምክኒያት በየስብሰባዎቹና በተለያዩ ጊዜያት ያንፀባረቀችው የትግል መስመር ነው። ይኼ የያዘችው የትግል መስመር በመላው ዓለም በአምባገነን በሚገዙ አገሮች ላይ ተሞክሮ አጥጋቢ ውጤት ያመጣ፣ የተሞከረበት የእያንዳንዱ አገር ሕዝቡ ራሱን ከአምባገነን አገዛዝ ነፃ ያወጣበት፣ አንደንዶቹም አምባገነኖች በማይታመን ፍጥነት የተንኮታኮቱበት ሁኔታ የታየበት ነው። በጄን ሻርፕ ተፅፎ (አልበርት አነስታይን ኢንስቲትዩት) በ3 ኢትዮጵያዊያን አገር ወዳዶች በአማርኛ የተተረጎመው‹‹ ከአምባገነን አገዛዝ ወደ ዲሞክራሲ ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ለነፃነት›› በሚለው እንደተገለፀው ‹‹ በዓለም ላይ የተለያየ መልክ ያላቸው አምባገነን መንግስታት በሕዝብ አልታዘዝም ባይነት እየተፍረከረኩ በአፍጢማቸው ተደፍተዋል። ሕዝቦች በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና በማህበራዊ መስክ የሚያሳዩትን አልታዘዝም ባይነት ለመቁዋቁዋም ክንዳቸው ሲዝልና ጉልበታቸው ሲብረከረክ ይስተዋላሉ። ›› ይልና በምሳሌነት የተለያዩ አገሮችን ተሞክሮ ይዘረዝራል።( መፅሀፉ በ albert einstein institute ዌብ ሳይት ውስጥ የተቀመጠ ስለሆነ ፈልጎ ማንበቡ እጅግ ጠቃሚ ነው።) ብርቱካንም የትግል አቅጣጫዋ ይኸ መሆኑ በግልፅ ታይቶአል። እንግዲህ አቶ መለስም ይኼ አደጋ ስለታየውና ሃሳቡ በህዝቡ መሃከል ከሰረፀ ባላሰበው ፍጥነት እንደሚያንኮታኩተው ስለገባው ነው ቶሎ ብሎ እስር ቤት የከተታት። ሌላም ማንም ሰው እንዳይጠይቃት የሚያደርገውም

ለዚሁ ብሎ ነው፡፡ አንድ ብርቱካን አሰበችው ብሎ ይኼንን ያህል ከራደ እንግዲያውስ ሁላችንም እንደእርስዋ ብናስብ እንዴት ይሆናሉ?

አሁን ባለው ያገራችን ሁኔታ ሌላ አማራጭ የተሻለ አማራጭ አይታይም፡፡ በመተባበር ይሄኑ የትግል መስመር በመከተል ይሄንን አምባገነን ስርዐትና በዙሪያው የተሰበሰቡ አሻንጉሊት ፓረቲዎችና ግለሰቦችን እናስወግድ፡፡ ከእንግዲህ ነፃነት የሚገኘው ከምርጫ ሳጥን ሳይሆን ከህዝብ እንቢ ባይነት እንደሆነ ማወቅ አለብን፡፡ ትግሉ በባህሪው አንባገነን የሆነ አገዛዝ ያለውን የመሳሪያና የሰው ሃይል እንኩዋን መጠቀም እንዳይችል የሚያደርግ የትግል ስልት ነው፡፡ ትጥቁን ከመፍታት ውጭ፡፡ ሆኖም ግን እንዲህ ቀላል ትግል አይደለም ‹‹ አምባገነን የማስወገድ ትግል›› ነውና፡፡ እንግዲህ በዚህ ሃሳብ የምንስማማ ከሆነ የኔን ሀሳብ ልግለፅና የጠለቀ ልምድ ባላቸው ተጠናክሮ ይቀጥላል ማለት ነው፡፡

ብርቱካን ትፈታ በማለት ብቻ ጊዜአችንን አናጥፋ፡፡ ይሄንንማ የወያኔ ደጋፊዎችም ያደርጉታል፡፡( የትግሉን መስመር እስካሳተላቸው ድረስ) ሆኖም ይኼንንም ሳንተው ማድረግ የምንችለው የብርቱካንን የትግል ስልት የራሳችን በማደረግ ትግሉን መቀጠል ነው ፡፡ ብርቱካን ምልክት ትሁን፡፡ በእያንዳንዱ ትግል ውስጥ እርስዋን ማሰብ ይገባል፡፡ ማንዴላችን ነች ካልን በተግባር መሆን አለበት፡፡ ወያኔ በሚፈልገው አይነት የብጥብጥ መስመር ውስጥ በምንም ዓይነት መግባት አያስፈልገንም፡፡

በአሁን ሰዐት መደረግ አለባቸው ብዬ የማስባቸው፡- ወያኔም ሆነ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ስብሰባ ሲጠሩ በብዛት መሄድና ማንኛውም ሰው መድረክ ላይ ወጥቶ ለመናገር ሲዘጋጅ በአንድ ላይ ጀርባን ለመድረኩ ሰጥቶ መቀመጥ፣ እጅን በአፍ ላይ ማስቀመጥ፣ ወይም ሁለት  እጅን ወደላይ በማውጣትና አመሳቀሎ ማሳየት (እንደታሰረ ሰው)፣ ምንም ድምፅ አለማሰማት እንዲሁም ተመሳሳይ የሆኑ ራስን የሚያቅቡ እርምጃዎችን መውሰድ፡፡ ጀርባን ለመድረኩ ሰጥቶ መቀመጥ በተቃዋሚዎች ላይ ለምን? የሚል ካለ፣ ይኼ የሚጠቅመው

1ኛ፡- በተቃዋሚዎች የሚጠራው ስብሰባ ከወያኔ ቁጥጥር የላላ በመሆኑ በቀላሉ ራስን መፈተሸ ያስችለናል እንደ ሰደድ እሳት በአንዴ ስለሚዛመትም በሚቀጥለው ጊዜ ብዙ ደጋፊ ያገኛል፣

2ኛ፡-የኛ ችግር የሚፈታው የነሱ ም/ቤት በመግባት አለመሆኑን ለማሳየት፣

3ኛ፡-የፖለቲካ ምህዳሩ ጠበበ፣ ሰዎቻችን ታሰሩ፣ በቀሪው ዓለም እናሳጣዋለን፣ በማለት ተደናግረው እንዳያደናግሩንና ይሄንን የቃላት እንቶፈንቶ ትተው ከተኙበት ለማንቃትና እንደተራው ህዝብ በእምቢተኝነት ትግሉ እንዲሳተፉ ጥሪም ይሆናቸዋል፡፡( ከ14-18ዓመታት ተቃዋሚ ሆነው ግማሾቹም በምክር ቤት ጥሩ ጊዜ ስላሳለፉ አሁን ይህንን ጊዜ ለነፃነት ትግል ቢያውሉት ይጠቀማሉ እንጂ አይጎዱም፡፡)

ይሄ ድርጊት ወያኔንም ሆነ ተቃዋሚዎችን በከፍተኛ ደረጃ ስለሚያስበረግጋቸው ህዝቡን ወደብጥብጥ ለመከተት ከፍተኛ ጥረት እንደሚያደርጉ በመገመት ህዝቡን ወደዚያ እንዳይከቱት መጠንቀቅ፡፡( በተቃዋሚ ፓረቲዎች ላይ የሚወሰደው ይሄ ራስን የማቀብ እርምጃ ብቻ ወያኔን ከፍተኛ ፍርሃት እንደሚለቅበት አይጠረጠርም፡፡ ከዚህ ሌላ የተቃዋሚዎች ተወዳድሮ ምክር ቤት መግባትስ የሚፈይደው ነገር ምንድን ነው?) በየቤታችን ውስጥ ስንሆን በሬዲዮ እና ቴሌቪዥን የሚተላለፉ ፕሮፓጋንዳዎችንና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ክርክሮች ላለማዳመጥ ዘግቶ መቀመጥ፣ ኤልፓ ሰውን ተራ አስገብቶ መብራት እንደሚያጠፋው ሁሉ ራስን በራስ ተራ አስገብቶ በተመሳሳይ ሰዐትና ቀን መብራት አጥፍቶ መቀመጥ፣ የመራጮች ምዝገባ ጊዜ ስለሆነ መምረጥ የሚችለው ህዝብ በሙሉ ተመዝግቦ የምርጫ ካርዶችን መውሰድና የምርጫው ዕለት ወደ ምርጫው ጣቢያ ዝር አለማለት፣ የወያኔ ሰራዊት፣ካድሬዎችና የመሳስሉት ወከባ በእጅጉ ሊኖር ቢችልም ሳይደናገጡ ከቤት ሳይወጡ መዋል፡፡

በዚህ መንገድ ፍላጎታችን የህዝብ ነፃነት እንጂ የፖለቲካ ፓርቲዎች እየተቡዋደኑ በየ5ዓመቱ የሚገቡበት እንዳልሆነ ማሳየትና ስልጣናችንንም በእጃችን ማስገባት ይኖርብናል፡፡ ሁላችንም በየግላችን ቁርጠኝነቱ ካለን ማድረግ ይቻላል፡፡ አለበለዚያ ሁልጊዜ ተመሳሳይ እሮሮ እያሰማን በላያችን ላይ ጥቂት ተመሳሳይ ሰዎች እንዲሰለጥኑብን እየፈቀድን መኖር ይሆንብናል፡፡ በፖለቲካ ፓርቲዎች ፉክክር የሚመጣ ለውጥ ቢኖር የተከበሩ የምክር ቤት አባል መጨመር ብቻ ነው የሚሆነው፡፡ በምክር ቤቱም የምንሰማው አዲስ ነገር ወያኔ የሚሰራውን በደል በተለያዩ ሰዎች አንደበት ሲገለፅ መስማት ብቻ ይሆናል፡፡

‹‹ ተቃዋሚዎች›› ከዚህ የዘለለ ፍላጎት (ራዕይ) ሲያሳዩም አልታዩም፡፡ የህዝቡንም ስቃይ ለሰከንድ ሲያበርዱ አልታዩም፡፡ ስለሆነም ይሄንን የምርጫ አርቲ ቡርቲ ትተው ከህዝቡ ጋር በመተባበር ለመጪዋ ኢትዮጵያ የምክር ቤት ወንበር እንዲያስቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከላይ በተጠቀሱትና በተጨማሪ በትግሉ መሃከል በሚያጋጥሙ የትግል ስልቶች በመጠቀም ስልጣኑን በህዝብ በእጅ ማስገባት አማራጭ የለውም፡፡ የወያኔን የተለያየ የማስፈራራት፣ የስም ማጥፋትና ሽብር መንዛት ተቁዋቁሞ በፅናት በመታገል፡፡ እዚህ ላይ በጄን ሻርፕ ተፅፎ በ3ቱ ኢትዮጵያውያን ከተተረጎመው መፅሀፍ ላይ ያገኘሁትን ማስገባት እወድዳለሁ፡፡‹‹ ዲሞክራቶች የራሳቸውን ችሎታ ብቃት በብቃት መተግበር ሳይችሉ አምባገነን መሪዎችን ለማስወገድ መመኘት የለባቸውም፡፡

ታዲያ ይኸ እንዴት ነው እውን መሆን የሚችለው? በምን ዓይነት ዓቅም ነው ዲሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ሃይሎች አምባገነኖችን ከጦራቸው፣ ከፖሊሰና ከስለላ ተቋዋሞቻቸው ጋር ከስልጣን ለማውረድ የሚችሉት? እነዚህን የፖለቲካዊ አቅም ማግኛ ጥያቄዎችን ለመመለስ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የ14ኛውን ክፍለ ዘመን የቻይና ተረት ማየት ይጠቅማል፡፡

ቹ በምትባል የቻይና ግዛት ውስጥ ዝንጀሮዎችን በማሰማራት የሚኖሩ አንድ አዛውንት ሰው ነበሩ፡፡ የሚተዳደሩትም ዝንጀሮዎቹ ከዚህም ከዚያም ለቃቅመው በሚያቀርቡላቸው ፍራፍሬ ነበር፡፡ የአገሬው ሰዎች የዝንጀሮዎች ጌታ ይሉዋቸዋል፡፡ ሁልጊዜ ጥዋት ጥዋት ዝንጀሮዎቹን በግቢያቸው ውስጥ ይሰበስቡአቸውና ከሁሉም ጠና ያለውን ዝንጀሮ መርጠው በማዘዝ ሌሎቹን በመምራት ወደጫካ ኼደው ከየዛፉ ላይ ፍራፍሬ ለቅመው እንዲያመጡ ያሰማሩአቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ዝንጀሮ ከአገኘው ፍራፍሬ ከአስር አንድ ለሰውዬው መስጠት ደንባቸው ነበር፡፡ ይህንን ማድረግ የተሳነው ዝንጀሮ ግን በሀይል ይገረፋል፡፡

በመሆኑም ሁሉም ዝንጀሮዎች በከፋ ሁኔታ ይሰቃዩ ነበር፡፡ ግን አንዳቸውም የተቃውሞ ድምፃቸውን አሰምተው አያውቁም፡፡

አንድ ቀን አንዱ ትንሽ ዝንጀሮ ‹‹ ለመሆኑ የፍራፍሬ ዛፎቹን የተከለና ያበቀለ ይኼ ሰውዬ ነው?›› በማለት ሌሎቹን ጠየቃቸው፡፡‹‹ እርሱ አልተከላቸውም በተፈጥሮ የበቀሉና ያደጉ ናቸው፡፡›› አሉት፡፡ ‹‹ ካለ አዛውንቱ ፈቃድ እነዚህን ፍራፍሬዎች መውሰድ አንችልም?›› አላቸው፡፡ ‹‹ አዎ! እንችላለን፡፡›› አሉት፡፡ አሁንም ቀጠለና ትንሹ ዝንጀሮ ‹‹ ታዲያ ለምንድነው አዛውንቱ እጅ ላይ የወደቅነው?›› ‹‹ ለምንስ እናገለግለዋለን?›› ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ ሁሉም ዝንጀሮዎች ነገሩ ተገልፆላቸው ባነኑ፡፡

በዚሁ ዕለት ማታ አዛውንቱን እንቅልፍ ሲወስዳቸው ዝንጀሮዎቹ ወደሚታጎሩበት ቦታ የሚወስዱትን መንገዶችና የሚታጎሩበትን ግቢ በሙሉ ያፈርሳሉ፡፡ ከዚያም እነርሱም የሰበሰቡትንን አዛውንቱ ያከማቹትን ፍራፍሬ ጥርግርግ አድርገው በመውሰድ ወደ ገደላቸው ይሄዳሉ፡፡ ከዚያም እስከ መጨረሻው ወደ አዛውንቱ አልተመለሱም፡፡ አዛውንቱም በረሀብ ሞቱ ይባላል፡፡ ይህ ተረት የተገኘው ዩ-ዚ-ሊ/ እ.ኤ.አ./ 1311-1375/ ካዘጋጀው መፅሀፍ ነው፡፡/

ታዲያ አንዳንድ መሪዎች ሕዝባቸውን በትክክለኛው መንገድ ሳይሆን እንደ ዝንጀሮዎቹ ጌታ በማታለል ያስተዳድራሉ፡፡ ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች የዝንጀሮ አሳዳሪው አይነት አይደሉም ወይ? አእምሮአቸው ልክ እንደማይሰራ የሚገነዘቡ አይደሉም፡፡ በመጨረሻም ሕዝቡ በማጭበርበር እንደሚገዙት ሲነቃባቸው ያ ያታለሉበት ዘዴ እንደሚከሽፍ አያውቁም፡፡

ነገሩ ቀላል ነው፡፡ አምባገነኖች የሚገዙትን ሕዝብ ድጋፍ ይፈልጋሉ፡፡ ካለ ሕዝቡ ድጋፍ የፖለቲካ ስልጣናቸውን ባስተማማኝ ሁኔታ ማረጋገጥ ይሳናቸዋል፡፡›› ከገፅ 18-19 (20-21)

ከዚህ በላይ በተገለፀው መፅሀፍ ውስጥ እንደተገለፀውና በግልጽ እንደሚታየው በርካታ የሆኑ በተግባር ላይ ውለው ውጤት ያመጡ በርካታ ዘዴዎች ሰፍረዋል፡፡ ለአገራችን ሁኔታ የሚስማሙትን እየመረጥን ብንጠቀምባቸው በአጭር ጊዜ ይህንን የአምባገነኖች ስርዓት መንግለን እንጥለዋልን፡፡በ97ቱ ምርጫ ወቅት ፐ/ር መስፍን በማይገባው ቁዋንቁዋ እናነጋግረዋለን ያሉትም ይህንኑ ነበር፡፡ (ከሰማይ በታች በማንኛውም ነገር ላይ ለመደራደር ዝግጁ ነኝ ያለውን ያስታውሱአል፡፡ በሌሎች አገሮች ተሞኩሮ ያመጣውን ውጤት ስላየ ነበር ቀበቶውን ያስፈታው፡፡ boycottቱ ሲቀርለት ደግሞ ያደረገው ታይቶአል፡፡)

እንግዲህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትንና ተመሳሳይ የሆኑ እርምጃዎችን በተቀነባበረ ዘዴ ከአከናወንን በአጭር ጊዜ የሰላም ዓየር እንተነፍሳለን፡፡ ከዚያ በሁዋላ የሚደረጉ የምርጫ ውድድሮችንም በበላይነት እንቆጣጠራለን፡፡ ለዚሁ ስራ እንዳይውሉ በአገር ውስጥ ያሉ መገናኛ ብዙሃን በህገወጥ አዋጅ ቢያዙም ከአገር ውጭ ያሉት በሰፊው ሊሰሩበት ይገባል፡፡ እከሌ እዚህ ፓርቲ ገባ እከሌ እዚያ ገባ፣ እከሌ ይቅርታ ጠይቁአል እከሌ አልጠየቀም፣ እከሌ ተለጣፊ ነው/አይደለም፣ እያልን እነዚህን ራሳቸውን ከውያኔ ዱላ መከላከል የማይችሉ አቅመቢሶች አንተማመን፡፡ ራሳችንን ከሁለቱም ቡድኖች አግዝፈን እንይ፡፡ እግዚአብሄር ኢትዮጵያን በቃሽ ብሎአት ይህንን ምርጫ በህዝብ የበላይነት የሚጠናቀቅበትና የአምባገነንነት ጊዜ ማከተሚያ ያድርግልን፡፡

www.ethiomedia.com – a site of alternative news and views